## ከሶምሶን አ. የተላከ ፩ኛ እ-ጦማር፡ -

*ይድረስ ለኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ።*

*ከዚህ ቀደም አጠር ያለ ጥያቄ በኀዋ ሰሌዳችን ላይ ያቀረብኩ ቢሆንም ምናልባት መላኪያውን ሳልሳሳት አልቀረሁም እና ደግሜ በዚህ መልእክት ልልክልዎት ሳስብ ተገቢውን ምላሽ እንደማገኝ በእግዚአብሔር ሙሉ እምነት በማሳደር ነው።*
*ይህም "እኔ የአባቱ- እህት -ባል- ወንድም -ልጅ የሆነችውን ማግባት እችላለሁ ወይ?" የሚል ነበር።*

## ከሶምሶን አ. ለተላከው ፩ኛ እ-ጦማር የተሰጠ መልስ፡-

ለጥያቄው፡ የምሰጥዎ መልስ፡ በመካከላችሁ፡ ምንም እንኳ የጋብቻ ዝምድና መኖሩ ቢታወቅም፡ የሃይማኖትና የምግባር፥ የአስተሳሰብና የሥርዓት አንድነት በታጣበትና በዚህ ረገድ፡ ጽኑ ችግር በተፈጠረበት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በኹሉም አግጣጫ የምትመስልዎ ኾና ከተገኘችና፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ጋብቻ ከተፈቃቀዳችሁ፡ የአክስትዎን ባል የወንድም ልጅ ለማግባት፡ ኢትዮጵያዊው የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታችን የሚፈቅድ መኾኑን ነው።

የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፡
ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ

## ከአዲስ አበባ፣ ከሶምሶን አ. የተላከ ፪ኛ እ-ጦማር፡

*ይድረስ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፡ ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ።*

*በልዑል እግዚአብሔር እና በእናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም የአክብሮት ሰላምታዬን አቀርባለሁ።*

*ከጓደኛዬ ጋር ብዙ ሲያሳስበን የነበረውን ምላሽ የያዘ መልእክትዎን በዕለተ ዑራኤል ደርሶኛል፤ እግዚአብሔር ይስጥልኝ!*

*በቀጣይ እንደእግዚአብሔር ፈቃድ በዚሁ አገልግሎትዎ የማልለይ ስሆን፡-*

*እያበረከቱት ላለው ታላቅ መንፈሳዊ አገልግሎትዎ እግዚአብሔር ዕድሜን ከጤና ጋር ይስጥልኝ።*

---

## ከአብርሃም የተላከ ደብዳቤ፡-

*"ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት" የሚለውን፡ የንቡረ እድ ኤርምያስን፡ ሦስተኛውን መጽሓፍ ብቻ አግኝቼ ለማንበብ በመብቃቴ፡ በአንድ በኩል፡ በጣም ደስ ሲለኝ፥ በአንድ በኩል ደግሞ፡ አንደኛውንና ኹለተኛውን መጻሕፍት ግን፡ ፈልጌ ላገኝ ባለመቻሌ፡ ቅር ተሰኝቻለሁ። አንዳንድ ጥራዝ ነጠቅ፡ መጤ 'ሃይማኖተኞች ነን!' ባዮች፡ ኢትዮጵያዊነትን በመካድ፡ በሚናገሩትና በሚያደርጉት፡ በጣም እያስገረሙኝ ናቸውና፡ 'ከቻላችሁ፡ ብትልኩልኝ!' እያልኩ፡ በኢትዮጵያዊነቴ ኮርቼ፡ ምስጋናዬን በማቅረብ እለምናለሁ።*

## ከአብርሃም ለደረሰን ደብዳቤ፡ የተሰጠ መልስ፡-

በተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች መናገሻ ከተማ፡ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ደብዳቤ ቤት አድራሻችን በኩል በላኩልን ክታብዎ ውስጥ የጠቀሷቸውን የኪስ ስልክዎን ቍጥርና በኢትዮጵያ፡ የደብዳቤ ቤት አድራሻዎ የኾነውን፡ መልእክት ሣጥን ቍጥር አክለን በመላክ፡ ለጥያቄዎ ተገቢውን ምላሽና ለፍላጎትዎ ተገቢውን አገልግሎት ያበረክቱዎ ዘንድ፡ ግዳጁንና አደራውን፡ በአዲስ አበባ ላሉት፡ የአገልግሎታችን ባልደረቦች ያስተላለፍን መኾናችንን እንዲያውቁት ይኹን።

---

## ከትምህርተ የደረሰን እ-ጦማር፡-

*"'ሉቃስ የሣላት' የተባለችው ይህች ሥዕል፡ ከአዝዋ ማርያም ገዳም ያመጧት ናት!" ብለው አንድ ሰው ሰጡኝ፤ እኔም፡ "እግዜር ይስጥልኝ!" ብዬ ተቀበልኋቸው። ታዲያ! ስለሥዕሏ ያሉኝ፡ ይህ ነገር፡ በእርግጥ እውነት ነወይ?*

## ከትምህርተ ለደረሰን እ-ጦማር መልስ፡-

ስለሥዕሏ፡ ከስጦታው አድራጊው የተነገረው ቃል፡ ከሌሎቹና እኛም ተቀብለነው ከኖርነው፡ የምስለ ፍቁር ወልዳ (ከተወዳጅ ልጇ ጋር) ከሚለው ሥዕል

የተለየች የሚያደርጋት፡ ጌታን በቀኝ ክንዱ የታቀፈችው መኾኗ ነው። በዚህ ሥዕል፡ እመቤታችን የምትገኘው፡ ከልጇ፡ በስተግራ መኾኑ ነው፤ ይህ ደግሞ፡ "ወትቀውም ንግሥት በየማንከ!" ማለትም፡ "ንግሥት፡ በቀኝህ ትቆማለች!" የሚለውንና የዚህን ቃል በተከተለው፡ በእኛ ሃይማኖታዊ ሥርዓት፡ እመቤታችን፡ በልጇ ስቅለት ጊዜ፡ ቆማ የነበረው፡ በመስቀሉ ቀኝ እንደነበረ፡ በትውፊት ሲነገር የኖረውን፡ የቅዱስ መጽሓፍን ቃል የሚቃረን ይኾናል።

ይኹን እንጂ፡ በእኛ እምነት፡ ዋናው ቁም ነገር፡ እንደጌታ ቃል፡ "በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ" የምንፈጽመውን አምልኳችንን፡ መሥርተን የምናካኺደው፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃል፡ በየልቦናችን ጽላት ላይ የተቀረጸውን መንፈሳዊዉን የምስለ ፍቁር ወልዳን ረቂቅ ሥዕል እንጂ፡ እውነት ይኹን ሓሰት፡ ተረጋግጦ ሊታወቅ የማይቻለውን፡ እከሌ የሣላት የሚባለውን፡ በሰው እጅ የተሣለውን ስላይደለ፡ ይህን የመሰለው ጉዳይ፡ እምብዛም አያሳስበንም።

---

## ከክብረ ማርያም የተላከ ፭ኛ እ-ጦማር፡-

*ከሰላምታዬ በመቀጠል ከብዙ ጥያቄዎቼ ውስጥ አንዷት ግራ የገባኝ ጥያቄ አለኝ እና ግዜ ካለዎት እንደው ቢመልሱልኝ ብዬ ነው፡፡ ጥያቄየም እንደሚከተው ይሆናል፡- አንድ ክርስቲያን ወደቤተ እግዚአብሔር /ቤተ ክርስቲያን/ የሚሄደው ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል ብቻ ነውን? "ቅዱስ ቁርባንን ካልተቀበልን ወደ ቤተ ክርስቲያን ብንሄድ ባንሄድ ምን ይጠቅመናል?" ይላሉ፡ አንዳንድ ሰዎች፤ "ካልቆረብኩኝ፡ ቅዳሴ መሄድ ምን ያደርጋል?" እያሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን አይሄዱም፤ የቁርባን ቀን ግን ቀድመው ይገኛሉ፡፡ ይሄንን ጥያቄ ቢመልሱልን፡ "ወደቤተ ክርስቲያን ካልቆረብኩኝ አልሄድም!" ለሚለው ሰው አስነብበው ነበር፡፡*

## ከክብረ ማርያም ለተላከው ፭ኛ እ-ጦማር፡ የተሰጠ መልስ፡-

ላቀረቡልኝ ጥያቄ መልሱ፡ “አዎን! አንድ ክርስቲያን፡ ወደቤተ እግዚአብሔር የሚኼደው፡ ቅዱስ ቍርባንን ለመቀበል ብቻ ነው።” የሚል ነው። ይህም፡ በተለየ ሥርዓት፡ ለምሳሌ፡ ክርስትናን፥ ተክሊልን፥ ወይም፡ ፍትሓትን በመሰለው ላይ እንዲካፈል ተጋብዞ ካልኾነ፥ ወይም፡ መካፈል ያለበት ኹኖ ካልተገኘ በቀር ማለት ነው። “የተለዩ ሥርዓቶች” በተባሉት፡ በእነዚህ ላይ በተገኘም ጊዜ ቢኾን፡ ሊቀበል አግባብ ነው፤ በዚህ ምግባሩ፡ ይህ ሰው፡ የዚያ ሥርዓት ተካፋይነቱን፡ ፍጹም እግዚአብሔራዊና እውነተኛ አደረገው ማለት ነው። ራሱንና ሰዎችን ብቻ ሳይኾን፡ እግዚአብሔርንም አስደስቷልና።

የምእመናንና የምእመናት ጉባኤ የተቋቋመው፥ በዚያ የሚሰባሰቡትም፥ ደግሞም፡ የቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ የተሠራውና ካህናቱ በዚያ የተሠየሙት፡ ታዲያ

ለምንድር ነው? ብቸኛውና ዋናው ዓላማኮ፡ ቅዱስ ቍርባንን ለማዘጋጀት፥ ለመቀበልና ለማቀበል ነው። ሌላ ዓላማ የለም። ያ ቤተ ክርስቲያን፡ የእግዚአብሔር ማዕድ ተሰናድቶና ተዘርግቶ የሚቀርብበት አዳራሽ ነው። ወደዚያ አዳራሽ፡ ተጠርተውም ኾነ ሳይጠሩ፡ ማለትም፡ ተጋብዘውም ኾነ፡ ሳይጋበዙ መኼድ፡ የተዘጋጀውን ማዕድ ለመሳተፍ ብቻ አይደለምን? አዎን! ነው።

ለዚህ ዓላማና ተግባር፡ ማለትም፡ ለመቍረብ ካልኾነ በቀር፡ ታዲያ! ሰው ኹሉ፡ ለምን ብሎ ነው፡ ወደቤተ ክርስቲያን የሚኼደው? ምናልባት፡ ብዙዎች፡ ሊሉት እንደሚፈልጉት፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ በጸሎት ለመነጋገር ከኾነ፡ እርሱን፡ ፈጣሪንማ፡ እየራሳችን፡ በእውነት የምናመልከው ከኾነ፡ እርሱ ደግሞ፡ በመንፈስ ቅዱስነቱ፡ ያለማቋረጥ፡ በየአፍታዋ፡ በውስጣችንም፥ በቤታችንም፥ ወይም በለንበት ቦታ ኹሉ የምናገኘው አይደለምን? አዎን! ነው።

በቤተ መንግሥት ኾነ፥ በየግለሰብ ቤት በሚዘጋጀው ግብር፥ ወይም ድግሥ ላይ፡ ተጠርቶም ኾነ ሳይጠራ ሊገኝ፡ ወደዚያ ገበታ የኼደ ሰው፡ ከዚያ ግብዣ፡ በመብላትና በመጠጣት ሳይሳተፍ የሚመለስ ይኖራልን? አይኖርም። የማይሳተፍ ከኾነማ፡ ቀድሞውንም አይመጣም፥ በግብዣውም ላይ አይገኝም። ማንም ሰው፡ ባዘጋጀው ድግሥ ላይ የተገኘለት ተጋባዥ፡ ሳይበላና ሳይጠጣ ቢመለስ፡ በዚያ ተጋባዥ፡ ማዘን ብቻ ሳይኾን፡ እንደሚቀየመው እርግጥ ነው፤ “የደገሠውን ሲበሉለት፥ የወለደውን ሲስሙለት!” የተባለውም ስለዚሁ ነው።

በተለይ እኛ፡ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች፡ ከእግዚአብሔር ባገኘነው የኑሮ ሥርዓታችን (ባህላችን) መሠረት፡ በእንግድነት ብቻ ሳይኾን፡ በዝምድና፥ ወይም በወዳጅነት፥ ወይም በጉርብትናም እንኳ ቢኾን፡ ሊጠይቀን፡ አዘውትሮ፡ የሚመጣውን፡ የምናውቀውንም ኾነ፡ የማናውቀውን፡ ማንኛውንም ሰው፡ በመብል መጠጥ ሳናስተናግደው መሸኘት እንደማንችል፡ በይፋ የታወቀ ነው። ያ ሰው፡ "አልጋበዝም!" ቢልም እንኳ፡ ይገደዳል እንጂ፡ መስተንግዶው ሳይደረግለት አይኼድም። ይህን ግዳጅ፡ "አሻፈረኝ! አልፈጽምም!" ብሎ፡ ቢኼድ፡ በእርግጥ ቅር ይለናል፤ እንቀየመዋለን ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ግን፡ ይህን የመሰለው ኹኔታ አይደርስም፤ ምክንያቱም፡ ኹለቱም ወገኖች፡ ባህሉን ስለሚያውቁትና ኹሉም፡ በየራሱ ስለሚያደርገው ነው።

በቅዳሴ ጊዜ፡ በቤተ እግዚአብሔር ተገኝቶ፡ ሥጋወደሙን በማይቀበል ሰውም ላይ፡ ጋባዦቹ ኢየሱስ ክርስቶስና ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰሰማቸው ይህንኑ የመሰለ እንደሚኾን፡ በሃይማኖት መገመቱ፡ ለማንም አያዳግትም። ለዚህ ታላቅ ሥርዓት አፈጻጸም መመሪያ እንዲኾን፡ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ትምህርት፡ በማቴ. ፳፪፥ ፩-፲፬፤ ፳፮፥ ፳፮-፳፰። በሉቃ. ፲፬፥ ፲፭-፳፬ እና በ፩ቆሮ. ፲፩፥ ፲፯-፴፬ እንደተጻፈው መመልከቱ፡ የእውነታውን ግንዛቤ በበለጠ ለማስጨበጥ ይረዳል።

ቅዱስ ቍርባንን፡ አመችቶንና ተመችቶን፡ ዕድሉን የምናገኝ ከኾነ፡ በየዕለቱ ልንቀበለው ይገባል። ቀን የምንወስንበት ምክንያት ሊኖር አያስፈልግም። በቤተ

ክርስቲያን ተገኝተን ለማስቀደስ ፍላጎቱ ኖሮን፡ ይህንኑ ለመፈጸምን ከቻልን፡ መቀበሉ ለምን ይቅርብን? እንዳይቀርብን ማድረጉ ይበጀናል።

እርግጥ፡ ከተቀባዩ ቍጥር ብዛት የተነሣ፡ ምእመናኑን ኹሉ በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የማይቻል በመኾኑ፡ የሚደርስ ችግር ካለ፡ ለችግሩ መፍትሔ ኾኖ የተገኘው ደግሞ፡ የፈረቃ ሥርዓት ቢኾን፡ የመቀበል ተራው ያልደረሰው ምእመን፡ በቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ ሊያስቀድስ ቢፈልግ፡ ባይቀበልም እንኳ፡ እንደተቀበለ ስለሚቆጠርለት፡ በዚያ ቤተ ክርስቲያን መገኘቱ ተገቢነትና ተቀባይነት እንዳለው ተደርጎ ሊወሰድ ይቻላል።

ወደቤተ ክርስቲያን በመኼድ፡ የሚገኙት ሌሎች መልካካም ውጤቶች፡ ለምሳሌ፡ የሰዎች እርስበርስ መገናኘትና መተዋወቅ፥ መጨዋወትና መወያየት፥ መረዳዳትና መገባበዝ፥ በበጎ ሥራ መተባበርም፡ እነዚህን የመሰሉት ኹሉ፡ እንደተጨማሪና ኹለተኛ ቍምነገሮች ኾነው የሚታዩ እንጂ፡ ከቍርባን ጋር የሚተካከሉ አለመኾናቸው መታወቅ አለበት።

ይህ ማብራሪያ፡ ለቀረበው ጥያቄ መልስ እንደሚኾን ተስፋ አደርጋለሁ።

ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ።

## ከክብረ ማርያም የተላከ ፪ኛ እ-ጦማር፡-

*የላኩሎት ጥያቄ መልስ በሚገባ በተብራራ መልኩ ተመልሶልኛል፤ እግዜር ይስጥልኝ።*

*አሁንም ሌላ የሚያስፈልገኝ ሁለት ጥያቄን ልጠይቅዎት! በቶሎ መልስ ቢሰጡኝ በጣም ጥሩ ነው፤ ምክንያቱም ቶሎ መልስ ማግኘት ስላለብኝ፡፡*
*፩. አንዲት ሴት ከፀነሰች ጀምሮ ቅዱስ ቁርባን መቀበል ትችላለች? ቢያብራሩልኝ!*
*፪. አሁን ሌላው ጥያቄዬ፡ የፀነሰች ሴት ፀበል መጠጣትስ፥ እንዲሁም መጠመቅ ትችላለች?*

*ሁለቱን ጥያቄዎች ቢመልሱልኝ በጣም ደስ ይለኛል፤ በጣም ግራ እየገባኝ ስለተቸገርኩኝ ነው፡፡ ምክንያቱም፡ ድሮ እናቴ ስትናገር እንደምሰማት፡ "አንዲት ሴት ከፀነሰች፡ መቁረብም፣ ፀበል መጠጣት ሆነ መጠመቅ፡ አይገባትም!" ትለኝ ነበር እና ግልጽ አድርገው ቢያብራሩልኝ።*

## ከክብረ ማርያም ለተላከው ፪ኛ እ-ጦማር፡ የተሰጠ መልስ፡-

ያለፈው ጥያቄዎ፡ በጻፍሁልዎ መልስ፡ የተብራራልዎ መኾኑን የሚገልጸው እ-ጦማርዎ ደረሰኝ፤ እግዜር ይስጥልኝ!

አኹን ላቀረቧቸው፡ ለኹለቱም ጥያቄዎችዎ፡ መልሱ፡ "አዎን!" የሚል ነው፤ ይህም፡ "በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ክርስትና የተነሣች አንዲት ሴት፡ ከፀነሰች ጀምሮ፡ ራሷን፡ እንደማናቸውም ጊዜ፡ በንስሓ እያነጻች፡ ቅዱስ ቊርባንን መቀበል፥ ጸበል መጠጣትንና እንዲሁም መጠመቅ ትችላለች፤ አንዳችም የሚከለክላት ምክንያትና ሰበብ የለም!" ማለት ነው።

የዚህም ማብራሪያ፡ ከዚህ ቀደም፡ የሴትን የወር አበባ፥ ልጅ የመውለድንና አራስነትን በሚመለከት፡ በመጻሕፍቱና በደብዳቤ መልሶቼ የተሰጠውን ስለሚመስል፡ ሌላ ሓተታ የሚያስፈልገው አይደለም።

እናትሽ ሰምተው የተናገሩት ይህና ሌላውም፡ ይህን የመሰለው አጉል ልማድ ኹሉ፡ ቀድሞ፡ አረማውያኑ ባዕዳንና በመካከሉ፡ አሪታውያኑ አይሁድ፥ ኋላም፡ ኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን ያመጡብን ጣጣ እንጂ፡ እኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በቀጥታ፡ ከእግዚአብሔር ያገኘነው ሥርዓት አይደለም። አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ ከእግዚአብሔር አግኝተው ያወረሱን፡ የእኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሥርዓት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከቅድስት ድንግል ማርያምና ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ድረስ፥ እስከዛሬ፡ ጠብቀነው የኖርነው፥ ዛሬም፡ እየጠበቅነው ያለነው፥ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም ጠብቀነው የምንኖረው፡ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ያገኘነው፡ እውነተኛው ሥርዓት፡ ይኸው፡ አኹን ያለንበትና እየኖርነው ያለነው፡ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" በሚለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታችንና ምግባራችን የሚመራው ሕይወታችን ነው። ከዚህ ውጭ የምንከተለው፡ ባዕድ አምልኮና የሰው ሥርዓት የለም።

ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ።

---

## ከአዲስ አበባ ሓመረ ኖኖች የደረሰን ፩ኛ እ-ጦማር፡-

*መቸም በዋሽንግተን ዲ.ሲ. አካባቢ ታይቶ የማይታወቅ የመሬት ነውጥ፡ በቅርቡ መድረሱን በመስማታችን መደናገጣችን አልቀረም፤ ነገር ግን፡ እንኳን እግዚአብሔር ቀላል አድርጎ አሳለፈው! አኹንም፡ ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ ድንግል ማርያም፡ በያለንበት፡ በምሕረታቸው አይለዩን!*

*ለመኾኑ፡ ከዚያ፡ ከነውጡ በኋላ፡ የኾነ ነገር የለምወይ?*

## ከአዲስ አበባ ሓመረ ኖኖች ለደረሰን ፩ኛ እ-ጦማር፡ የተሰጠ መልስ፡-

የደረሰው የመሬት ነውጥ፡ አንዳንድ ቀደምት ምልክቶችን በማግኘትና በማጤን ስናወጣ ስናወርደው የነበርነው የማይቀር ትንግርት ስለነበረ፡ ሌሎቹን፡ ያልጠበቁትን ወገኖች ባስደነገጣቸው መጠን፡ እኛን፡ ያን ያህል የነካን አልነበረም።

በዕለቱ፡ ለጥርስ ሕክምና ቀጠሮአችን ለመድረስ፡ በራሳችን ተሽከርካሪ ቀደም ብለን ወጥተን፡ እግረ መንገዳችንን፡ ልናልፍበት ወዳቀድነው መሥሪያ ቤት እያመራን ሣለን፡ ለካ፡ በሠፈራችን ያለውንና የምናውቀውን መንገድ ስተን ኖሮ፡ እንደዚያ እየተጓዝን መኼዳችንን መገንዘብ አቅቶን፡ ኋላ፡ እውነታውን ስንረዳ፡ ከዚያ ከሳትነው መንገድ ለመውጣት ተሥኖን፡ ስንባዝን ቆይተን፡ በመጨረሻ፡ አያሌ ደቂቃዎችን አባክነን፡ ወደዋናው ትክክለኛ መንገዳችን ለመመለስና ከዚያ መሥሪያ ቤት ለማሳተም ቻልን።

ይኹን እንጂ፡ በዚህ ጊዜ፡ የሕክምና ቀጠሮአችን ሰዓት ስላለፈ፡ በሰዓታችን ለመድረስ የማንችል መኾናችንን ስንገነዘብ፡ ለሕክምና ቤቱ ስልክ ደውለን አስታወቅናቸው፤ በእነርሱም በኩል፡ ጥያቄያችንን ስለተቀበሉን፡ መንገዳችንን ወደእነርሱ ቀጠልን፤ ይህ ኹሉ ሲኾን፡ በእኛ በኩል፡ ምንም ያስተዋልነውና የተረዳነው ነገር አልነበረም።

ከሃያ ደቂቃዎች በኋላ፡ ከሕክምና ቤቱ ደርሰን ስንገባ፡ ሓኪሞቹና ሠራተኞቹ ኹሉ፡ በታላቅ ድንጋጤ ተውጠው፡ ደኅና በመኾናቸው ብቻ፡ ከፍተኛ መጽናናት ተሰምቷቸው፡ ባልተለመደ ኹኔታ እያቀፉን ተገናኘን።

እኛም፡ ግራ ገብቶን፡ እየሳቅን ልናነጋግራቸው ስንሞክር፡ እነርሱ ግን፡ በዚያው በድንጋጤ ገጽታቸው እንደተዋጡ ኾነው፡ "ምንም ነገር አልኾናችሁም? አልሰማችሁም? አላያችሁም?" እያሉ ሲጠይቁን፡ "ኧረ! ምንም የኾንነው፥ ያየነውና የሰማነውም ነገር የለም!" ካልናቸው በኋላ፡ የደረሰውን የመሬት ነውጡን፥ ያም፡ የቱን ያህል ከባድ እንደነበረ፡ ሲቃ ይዟቸው አጫወቱን።

<u>ስለዚህ፡ በዚህ ረገድ የኾነውን ኹሉ የሰማነው፡ በሩቅ እንዳልላችሁት፡ እንደእናንተው መኾኑን እንድታውቁት ይኹን!</u>

ነገሩ፡ እንዲህ መኾኑን እንደተረዳን፡ ወዲያው፡ የእምነትና የሕይወት ወገኖቻችን ወደኾኑት ወደቅርቦቹ ቤተሰቦች ብንደውል፡ የኪስና የቤት ስልኮቻቸው፡ በሙሉ ሊሠሩ ስላልቻሉ፡ ወደመኖሪያ ቤታቸው ኼዶ፡ እነርሱ የሚገኙበትን ኹኔታ ማጣራት አስፈለገ።

ከዚህ የተነሣ፡ የተቀጠርንበት ሕክምናችን እንዳበቃ፡ ከዚያ ተነሥተን፡ እቤታቸው ስንደርስ፡ በነውጡ ጊዜ፡ ቤተሰቡ ኹሉ፡ ለየብቻቸው፥ ከሕፃናቱ ጋር ያሉትም፡ በልጆች መጫወቻ ሜዳ ላይ፡ ከቤታቸው ውጪ እንደነበሩ፡ ወደቤት ተመልሶ ያገኘነው አባወራ ነገረን።

የሥነ ፍጥረቱ ሠሪና አስገኚ፥ ባለቤትና ተቆጣጣሪ የኾነው፡ ኃያሉ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስና የዚህ መለኮታዊ የምሕረት ቃል ኪዳኑ ሕያው ማኅተም የኾነችው ርኅርኅት እናታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ይህን የመሰለው ኹኔታ በሚደርስበት ጊዜ፡ የቀስተ ደመናውን ምልክት በያዘው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተማምነን የምንኖረውን፡ እኛን አማኞች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻቸውን፡ እንኳንስ ጉዳቱና ድንጋጤው ሊያገኘን ይቅርና፡ የደረሰ መኾኑንም እንኳ እንዳንሰማው እንደሚያደርጉ፡ በዚህና እስካኹን እያደረጉልን ባየነው ጥበቃቸውና በምናየው እንክብካቤያቸው አውቀነው እናምንባቸዋለን።

ስለዚህ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ያለን እምነታችንና ታማኝነታችን፡ በእኛ በኩል እንዳይጓደል ከመጠንቀቅ በስተቀር፡ በሌላው፡ "ምናልባት፡ ሊደርስ ይችል ይኾናል!" እንኳ ብለን፡ በማናቸውም ነገር እንዳናስብና እንዳንጨነቅ፡ በብርቱ ያስፈልገናል።

ከዚያም ወዲህ፡ የደረሰ ተከታታይ የጠንቅ ምልክት ስለሌለ፡ ለመለኮታዊው ማስጠንቀቂያ፡ ይህን ያህል ትኩረት የሰጠው ያለ መስሎ ከቶ አይታይም፤ የእግዚአብሔሩ ምሕረት የታየበት፡ ይኸኛው ማስጠንቀቂያ ቸል ተብሎና ተረስቶ፡ አኹን፡ በአገሩ ምሥራቃዊ ክፍል ላይ፡ በዚሁ ሳምንት መጨረሻ፡ ሊደርስ ስላንዣበበው፡ ታላቅ የዐውሎ ነፋስና ኃይለኛ ውሽንፍር ጥቃት፡ ሕዝቡና መንግሥቱ፡ በከፍተኛ ጭንቀት ተውጠው እየተራወጡና እየተዋከቡ ይገኛሉ።

እኛም፡ በመጻሕፍታችንና በኅዋ ሰሌዳችን፥ በደብዳቤዎቻችንና በሱባኤዎቻችንም አማካይነት፡ ተልእኳችንን የፈጸምንና እየፈጸምን ያለን መኾናችንን ብናውቅም፡ አኹንም፡ "አቤቱ! ይቅር በል!" እያልን መማፀናችንን ቀጥለናል። ይህን ግዳጃችንን ከመወጣት በቀር፡ ስለሚኾነውና ስለሚደርሰው አስፈሪ ነገር ኹሉ፡ እንኳንስ፡ እኛ ደካሞቹ፡ "የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!" ብሎ የተናገረ ፈጣሪና እናቱ ስላልተደመጡ፡ ምንም የቀረ የምናደርገው አስተዋጽኦ ባለመኖሩ፡እየራሳችንን፡ ከኀሊና ወቀሳ ጭምር ነጻ ያወጣን ይመስለናል።

---

## ከአዲስ አበባ ሓመረ ኖኆች የደረሰን ፪ኛ እ-ጦማር፡-

*ባዕዳን፥ በተለይም፡ ምዕራባውያን ሕዝቦች፡ (የዘመኑ ሥጋዊ ኑሮ ብክነት ባስከተለባቸው ግዴታ መነሻነት ይመስላል፡) የያገራቸው ባህል ኾኖ፡ "የአባቶች ቀን" እና "የእናቶች ቀን" እያሉ፡ በተለያየ ዕለት፡ በዓመት በዓልነት የሚያከብሩዋቸው፡ ኹለት ቀኖች መኖራቸው ይታወቃል፤ እነዚህ የባዕዳን በዓላት አከባበር፡ እንደታኅሣሡ የገናው በዓል ዛፍ ኹሉ፡ ምናልባት፡ በውጭ አህጉር ተበትነው በሚኖሩት ወገኖቻችን ላይ አንዳች ልዩ ተፅዕኖ ሊኖረው ስለሚችል፡ ይህ ባህል፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን አኳያ ምን ዓይነት*

*ግምትና አቀባበል ሊደረግለት እንደሚገባ መግለጡ አግባብ አይኾንምወይ?*

## ከአዲስ አበባ ሓመረ ኖኖች ለደረሰን ፪ኛ እ-ጦማር፥ የተሰጠ መልስ፡-

በዚህ እ-ጦማር አማካይነት የቀረበው መጠይቃዊ አስተያየት፡ ለኹሉም ወገኖቻችን የሚያስፈልግና የሚበጅ ስለመሰለን፡ ከዚህ በሚከተለው መልክ አቅርበነዋል፡-

በዓለሙ ኹሉ የተበተናችሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ማኅበራዊው ኑሮአችሁ እያስገደዳችሁ፡ ኹለቱንም በዓላት፡ ማለትም፡ "የአባቶች ቀን" እና "የእናቶች ቀን"፡ የሚባሉትን ዕለታት፡ እንደያገሩ ባህል፡ በያላችሁበት ማክበራችሁ እንደማይቀር ይታመናል፡፡

ይኹን እንጂ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በዚህ ረገድ፡ ከእግዚአብሔር፡ በቅዱሱ ኪዳን አግኝተን የኖርንበት፥ አኹንም እየኖርንበት ያለነው፥ ወደፊትም የምንኖርበት፥ ልንከተለው የሚገባንም፡ የሃይማኖት ሥርዓት ስላለን፡ ይህንኑ አውቃችሁት፡ በተግባር ላይ ማዋላችሁን ትቀጥሉበት ዘንድ እያሳሰብናችሁ፡ ይህን የመሰለውን ሕያው ቅርሳችንን የሚያጸኑ፡ ከዚህ የሚከተሉትን ቍምነገሮች፡ በአጫጭር አውስተንላችኋል፡-

፩ኛ፡ በሥጋ ወላጆችና ተወላጆች መካከል ያለው የፍቅር ግንኙነት፡ ገና፡ ከልደት ጀምሮ፡ በዓመቱ ሰዓታትና ዕለታት፥ ወራትም ብቻ ሳይኾን፡ ያለማቋረጥ፡ ለዘለዓለም ሲታወስና ሲከበር የሚኖር እንጂ፡ በዓመት፡ ለአንድ ቀን ብቻ ተወስኖ የሚከበር ስላይደለ፡ እኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ስንፈጽመው እንደኖርነው ኹሉ፡ ዛሬና ወደፊትም፡ አባቶችና እናቶች፡ ለልጆቻችን፡ በአግባቡ፡ ያደረግነውን በመከተል፡ ልጆችም፡ ለአባቶቻችንና ለእናቶቻችን ያለንን ፍቅርና አክብሮት፥ ትሕትናና ታዛዥነት፥ ጥንቃቄና እንክብካቤ፡ በየአፍታው መቀጠሉ ይጠበቅብናል፡፡

፪ኛ፡ "አባት!" ወይም፡ "አባታችን!" ብለን የምንጠራውና በዚህ ማንነቱ፡ በዓመቱ ውስጥ፡ በስሙ እንድናከብራቸው በዓላትን የመደብንለት፡ አባት ወይም አባታችን፡ አንዱ ልዑል እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

፫ኛ፡ "እናት" ወይም፡ "እናታችን!" ብለን የምንጠራትና በዚህ ማንነቷ፡ በዓመቱ ውስጥ፡ በስሟ እንድናከብራቸው በዓላትን የመደብንላት፡ እናት ወይም እናታችን፡ አንዲቷ የአምላክ እናት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ ናት፡፡

፬ኛ፡ እኛ፡ የሥጋ ወላጆችና ተወላጆች፡ ከእግዚአብሔር፡ በሥጋና በነፍስ ተፈጥረን፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ከእርሱ የተወለድን በመኾናችን፡ ኹላችንም፡ የእርሱ፡ የአንዱ አባታችን ልጆች ነን፡፡

፭ኛ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ለእኛ፡ የዘለዓለማዊ ሕይወትን ዘውድ ሊያቀዳጀን፡ ከሰብአዊት እናት፡ በሰውነት ተወልዶ፡ እኛንም፡ የሥጋ ወላጆችንና

ተወላጆችን፡ የቅድስት እናቱ፡ የድንግል ማርያም ልጆች ስላደረገን፡ ኹላችንም፡ የእርሷ፡ የአንዲቷ እናታችን ልጆች ነን፡፡

፮ኛ፡ “አባትህንና እናትህን አክብር!” የሚለው መለኮታዊ ትእዛዝ፡ ለሥጋ ተወላጆች የተሰጠው ለምን እንደኾነ፡ በትክክል መረዳት ያስፈልገናል፤ ይኸውም፡ የሥጋ ወላጆች፡ የእውነተኞቹና የዘላለማውያኑ አባትና እናት፡ የልዑል እግዚአብሔርና የድንግል ማርያም፡ ባለአደራዎችና ተጠሪዎች በመኾን፡ በሥጋ የወለዷቸውን ተወላጆች፡ በጥንቃቄና በእንክብካቤ እንዲያሳድጓቸው መኾኑን በማመን፡ የሥጋ ወላጆችም ኾኑ፡ ተወላጆች፡ ይህን፡ ኃላፊነታቸውን አውቀውት፡ ግዴታቸውን፡ በየፊናቸው እንዲወጡ ሊያሳስብ ነው፡፡ (ማቴ. ፲፭÷ ፩-፱፡፡)

፯ኛ፡ “አባታችሁ አንዱ÷ እርሱም፡ የሰማዩ ብቻ ነውና፡ በምድር ላይ፡ ማንንም፡ “አባት!” ብላችሁ አትጥሩ!” የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ መጠበቅና መከበር÷ መፈጸምም እንዳለበት፡ ምንጊዜም፡ ሊታሰብ ይገባል፡፡ (ማቴ. ፳፫÷ ፱፡፡)

---

## ከአዲስ አበባ ሓመረ-ኖኖች የደረሰን ፫ኛ እ-ጠማር፡-

*በፈረንጆቹ ቀን አቈጣጠር፡ በኤፕሪል ፳፱÷ ፪ሺ፲፩ (April 29, 2011 ስለተፈጸመው፡ ስለእንግሊዝ ቤተ መንግሥታዊ ጋብቻ፡ ምን አስተያየት አላችሁ?*

*ወጣቶቹ፡ ንጉሣዊው መስፍን ዊልያም ፊሊፕ (Prince William Philip) እና ሕዝባዊቷ ወይዘሪት ኬት ሚድልተን (Ms. Kate Middleton) ደኅና አስተሳሰብና አመለካከት ያላቸው ይመስላሉ፤ ከተራው ሕዝብ ጋርም፡ መቀላቀል የፈለጉ ይመስላሉ፤ በቤተ ክርስቲያንም፡ የነበረው ሥርዓትና ንባቡ ኹሉ፡ ትምህርት ሰጪ ነው፤ በተለይ ለወጣቱ።*

*ነገር ግን፡ ቅዱስ ቊርባንን አልተቀበሉም፤ የኢየሱስ ክርስቶስንም እናት ስም፡ አንዴም ሲያነሡ አልሰማንም፤ ሙሽሪቷም፡ ቃለ መሓላ፡ እንደወንዱ (፪ ጊዜ) አልፈጸመችም፤ "ምናልባት፡ የእነርሱ ሥርዓት፡ እንዲህ ቢኾን ይኾናል!" ብለን አሰብን። እንደእኛና እንደሌሎቹ የጥንት ሕዝቦች ባህል፡ "እልል!" ማለት ስለማይችሉ፡ አልደመቀላቸውም እንጂ፡ ሥርዓቱ፡ ጥሩ ነበር።*

## ለአዲስ አበባ ሓመረ-ኖኖች ፫ኛ እ-ጠማር፡ የተሰጠ መልስ፡-

የሙሽራውን፡ ንጉሣዊ መስፍን ዊልያም ፊሊፕን እና የሙሽሪቷን ሕዝባዊት ኬት ሚድልተንን ጋብቻ መነሻ በማድረግ፡ ስለእንግሊዙ ቤተ መንግሥታዊ የሠርግ ሥርዓት ላወሳችሁት ቁም ነገር፡ ሰዓቱ፡ በዚያን ጊዜ፡ ለእኛ፡ በአሜሪካ እንገኝ

ለነበርነው፡ የሌሊቱ ክፍል ስለነበረ፡ ልንከታተለው አላመቻችንምና፡ አላየነውም። ስለሥርዓቱ ከሠነዘራችሁት በጎ አስተያየት ጋር፡ የታዘባችሁትንም መግለጻችሁ፡ "አበጃችሁ!" የሚያስሰኝ ነው።

ነገሩ ከተነሣ ዘንድ ግን፡ በተለይ እኛን፡ ኹላችንንም፡ የሚያስታውሰን ልዩ መልእክት እንደሚኖረው፡ አይጠረጠርም፤ ይኸውም፡ በዓለም ላይ ከሚገኘው የሰው ዘር መካከል፡ ወደኹለት ትእልፊት ተኩል (2.5 Billion) የሚጠጋው፡ ሥርዓቱን፡ በአካልና በነፋስ ሥዕል፥ በሌላውም የኀዋ አውታር አማካይነት፡ በጉጉትና በከፍተኛ የጋለ ስሜት ያየው ሲኾን፡ በዚህ ጊዜ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን ጨምሮ፡ ስንቱ ይኾን፡ ከእንግሊዛዊው ዘርና ከንጉሣዊው ቤተሰብ ባለመወለዱ የተቆጨ?! ወይስ፡ ይህን የመሰለ ኹኔታ በደረሰ ቍጥር፡ "ወይኔ! ምነው ይህን ከመሰለ ወገን በተወለድሁ ኖሮ! በተሻለኝ ነበርእኮ!" ብሎ የተመኘ ስንቱ ይኾን?

ደግሞስ፡ በዚህ አንጻር፡ እንዲህ፡ እንደእኛ፡ እንደቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከእግዚአብሔር፡ በነፍስም፥ በሥጋም፥ በመንፈስም በመፈጠሩና በመወለዱ፡ ከዚህ፡ ከዛሬው፡ ከሰብአዊውና ከምድራዊው፥ ከጊዜያዊውና ከዓለማዊው የእንግሊዞች ክብርና ደስታ ይልቅ፡ እጅግ ከፍ ያለው፡ ሉዓላዊውና ኹለንተናዊው፥ ዘለዓለማዊውና መለኮታዊው ክብርና ደስታ የተሰማው ሰብአዊ ፍጡር፡ ከወንዱም፥ ከሴቱም፡ ስንቱ ይኾን?

ይኸውም፡ "እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ሴቱም፥ ወንዱም፡ የፍጥረተ-ዓለሙ አስገኝና ባለቤት፥ ዘለዓለማዊ ጌታና አምላክ የኾነው፡ የእግዚአብሔር እና የቅድስት እናቱ የድንግል ማርያም ልጅ፥ የመንግሥታቸውም ወራሽ፡ ማለትም፡ ንጉሥ፥ ወይም፡ ንግሥት፥ ምሉክና ካህን የመኾኑን እውነታ ያወቀ፥ አውቆም፡ በእምነት የተቀበለው፥ ተቀብሎም፡ በዚህ ሕይወት የሚኖረው ስንቱ ይኾን?" ማለት ነው።

ይልቁንም፡ እንግሊዞችና በዓለም ላይ ተበትነው፡ የአገዛዙን ሥልጣን የያዙት፡ የእነርሱ ዝርያዎችና ግርፎች፡ ዛሬ፡ እነርሱ፡ በአገራቸው አስፍነውት፡ እየሠሩበትና እየተገለገሉበት፥ እየተጠቀሙበትና እየተደሰቱበት ያሉትን ይህንና ጠቅላላውን ሥርዓተ ሕዝብና መንግሥት፡ ከማንና ከየት ያገኙ ይመስላችኋል? ከቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትእኮ ነው? ታዲያ! እውነታው ይህ ኾኖ ሣለ፡ ይኹን እንጂ፡ የእኛን፡ የቀዳሚዎቹን ይዞታ እንዲጠፋ፥ የእራሳቸው የውሰት ውርስ ግን እንዲጸና በማድረግ የሚያካኺዱትን ረቂቅና ግልጽ ዘመቻቸውን የሚያውቀው፡ ስንቱ (ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት እና/ወይም፡ የሰው ዘር) ነው?

ይህን ኹሉ የሚያውቀው እግዚአብሔር አምላክ፡ በፍትሕ ርትዕ የምትፈጸም ፍርዱን ይሰጣል፤ አኹንም እየሰጠ ነው።

---